<u>**የህፃናት ምግብ ቁጥጥር ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ**</u>

<u>**መግቢያ**</u>

ከዚህ ቀደም ለማብራራት እንደተሞከረው የህፃናት ምግብ በልዩት ኩረት ለብቻው የህግ ማህቀፍ አውጥቶ መቆጣጠር ያስፈለገበት ዋነኛ ምክንያት ለህጻናት የሚቀርብ ምግብ ልዩ ጥንቃቄና ትኩረት ስለሚያስፈልገውና ህፃናትም ካላቸው በሽታን የመከላከል አቅም አናሳነት የተነሳ ለእነርሱ የሚቀርብ ምግብ የበለጠ ጥንቃቄና ቁጥጥር ሊደረግት የተገባበ መሆኑ ነው፡፡

በዋነኛነት ለህፃናት እድገት የእናት ጡት ወተት እጅግ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ሳለነገር ግን በፋብሪካ ደረጃ በሚዘጋጁ ምርቶች የተጋነነ ማስተዋወቅ ምክንያት እናቶች ከማጥባት እንዳይቆጠቡ ተገቢውን እንክብካቤ ለእናት ጡት ወተት ማድረግ በማስፈለጉና፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያዩ የማስታወቂያ መንገዶች የሚደረጉ አለአግባብ የተጋነኑ ማስታወቂያ በአርተፊሻል የወተት ምርት ላይ በማካሄድ ምክንያት እናቶች እንዳያጠቡ የሚደረገውን ዘመቻ ለመከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

በመሆኑም ባለስልጣን መ/ቤቱ በፊት ቁጥጥር ያድርግበት የነበረውን የህፃናት ምግብ ቁጥጥር መመሪያ ከአዲሱ የምግብ እና መድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ጋር በተጣጣመና የቁጥጥር ስርዓቱንም በጠነከረ በልኩ መቆጣጠር በማስፈለጉ የበፊቱ መመሪያ ሊከለስ ችሉዋል፡፡ረቂቅ መመሪያውም የህፃናት ምግብን አስመልክቶ የፌደራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቀጥር 1183/2013 መሰረት በረቂቁ ላይ ህጉ በሚያዘው መሰረት ሰፋ ያለ ውይይት በባለሙያዎች እና በሚለከታቸው የባለድርሻ አካላት ከተደረገ በኃላ በጋዜጣና በባለስልጣን መ/ቤቱ ድህረ-ገፀ ላይ ለህብረተሰቡ ለአስተያየት የወጣ ሲሆን፤ በመጨረሻም የመጡት አስተያየቶች ተካተው ለጠቅላይ ዐ/ህግ ለአስተያየት መላኩ የሚታወስ ነው፡፡

ጠቅላይ ዐ/ህግም በዋነኛነት ከሰጣቸው አስተያየቶች ውስጥ በረቂቅ መመሪያው መግቢያ ላይ መመሪያውን ለማውጣት የስልጣን ምንጭ የሆነውን አዋጅ ቁጥር

1112/2011 አንቀጽ 71(2) አስፈጻሚው መመሪያ ሊያወጣ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡በሌላ በኩል በአዋጁ አንቀጽ 2(57)ስር አስፈጻሚ አካልን ሲተረጉም ይህንን አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ህጎችን በፌዴራል ደረጃ ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው የፌዴራል መንግስት አካል መሆኑንና፣ነገር ግን ይህ አስፈጻሚ አካል የትኛው እንደሆነ በግልጽ በአዋጁ ውስጥ አልተካተተም የሚል ሲሆን፣ይህንንም በወቅቱ በተቋማቹ ከሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ጋር በመነጋገር የባለስልጣን መ/ቤቱ መቋቋያ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተልኮ ጋና ያልፀደቀ በመሆኑ አዲስ በተከለሰው የፌደራል አስፈፃሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀፅ (65) መሰረት የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለስልጣን ረሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አስፈፃሚ አካል ሆኖ በአዋጁ መሰረት ተቋሚል በሚል እንዲካተት ተደርጉዋል ፡፡

ሌሎች ተጨማሪ አስተያየቶች የተሰጡት ሲሆን አብዛኞቹ አስተያየቶች የአማርኛ አቻ ፍቺ ያላቸው የእንግሊዘኛ ቃላት በአማርኛ እንዲተረጎሙ፣ስርዓተ-ነጥቦች እንዲስተካከሉና ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው ፊደላት፣ቃላት እና አንቀፆች እንዲስተካከሉ የሚሉ ናቸው፡፡ረቂቁም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ተገቢውን ማስተካከያ ተደርጎት በባለስልጣኑ ከፍተኛ አመራሮች(ማኔጅመንት ኮሚቴ) በቀን 15/መስከረም,2014 ዓ.ም ቀርቦ በሙሉ ድምፅ ፀድቋል፡፡